

# ሙሴ

- ከዮሴፍ ሞት በኋላ በግብፅ ምድር ጨካኝ ገዢ ተነሳ። የዮሴፍ ቤተሰብ መብዛትና መበራከት ስጋት ውስጥ ከተተው። ስለዚህ እስራኤላውያንን ባሪያ በማድረግ በብርቱ ስራ እንዲጠመዱ አደረገ። በዚህም ከተሞችን ሰሩ። በተጨማሪም በእርሻ ሥራ ላይ ተሰማሩ። በተለይ ወንዶች ልጆች ካደጉ ወታደሮች ይሆኑና ይዋጉኛል ብሎ ፈራ። ስለዚህ ወንድ ልጆች ሲወለዱ እንዲገደሉ የሚል አዋጅ አዋጀ።

- ሙሴ ከተወለደ በኋላ ለ3 ወር ያህል እናቱ ሸሸገችው። .ከሶስት ወር በኋላ ግን ቅርጫት ሰርታ በወንዝ ላይ አስቀመጠችው። . የፈርኦን ልጅም አገኘችው። የሙሴ እህትም ሕፃኑን የሚያሳድገው ሞግዚት ልትፈልግ ሄደች። የፈርኦን ልጅም እንደራሷ ልጅ አድርጋ አሳደገችው።

- ካደገ በኋላ ግብፅን ለቆ ወደ ምድያም አገር መሄድ ነበረበት። አንድ ቀን በጎች እየጠበቀ ሳለ እንግዳ ራዕይን ተመለከተ። በቁጥቋጦ ውስጥ እሳት ይነዳል። ቁጥቋጦው ግን አይቃጠልም። እግዚአብሔር ከሚነደው ቁጥቋጦ ውስጥ ወደ ግብፅ ምድር እንዲወርድና እስራኤላውያንን ከፈርኦን ጨካኝ አገዛዝ ነፃ እንዲያወጣቸው ተናገረው። ሙሴ በጣም ፈራ። ሆኖም ግን ወደ ግብፅ ምድር ሄደ። ወንድሙ አሮንም አብሮት ነበር።

- ሙሴና አሮን ፈርኦንን ለማነጋገር ሄዱ። እግዚአብሔር እስራኤላውያን ከግብፅ ምድር እንዲወጡ እንደሚፈልግ ነገሩት። ፈርኦንም እግዚአብሔርን እንደማያውቀውና እስራኤላውያንንም እንደማይለቅ ነገራቸው። እግዚአብሔርም ለሙሴና ለአሮን ተአምራት የሚያደርጉበትን ኃይል ሰጣቸው። አሮን በትሩን መሬት ላይ ሲጥላት ወደ እባብ ተለወጠች። የግብፅ አስማተኞችም በትሮቻቸውን መሬት ጣሉ። እነሱም እባብ ሆኑ። ሆኖም የአሮን እባብ የአስማተኞቹን እባቦች ዋጠቻቸው። እግዚአብሔርም ኃይሉን አሳየ።

- ፈርኦን የእስራኤልን ሕዝብ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላልነበር አስር መቅሰፍቶች በግብፃውያን ላይ ወረዱባቸው። መቅሰፍት ማለት እጅግ በጣም መጥፎ ነገር ሲሆን ብዙ ስቃይንና ሞትን የሚያስከትል ነገር ነው። በመጨረሻም ከአስረኛው መቅሰፍት በኋላ ማለትም ፈርኦን የገዛ ልጁ ከሞተበት በኋላ እስራኤላውያንን ለመልቀቅ ተገደደ።

*ይህ የሙሴ ታሪክ በብሉይ ኪዳን በዘፀአት መፅሐፍ ከምዕራፍ 2 – 12 ድረስ ባለው ክፍል ውስጥ ይገኛል።*

http://gardenofpraise.com